# የፕሮጀክት መረጃ ሰነድ (ፕመሰ)

## ግምገማ ደረጃ

**የሪፖርት ቁጥር: ኤቢ2146**

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክት ስም | መሠረታዊ አገልግሎቶችን ማስከበር |
| አህጉር | አፍሪካ |
| ዘርፍ | አጠቃላይ የመንግሥት አስሪዳደር ዘርፍ (100 %) |
| የፕሮጀክቱ መታወቂያ | ፒ 074015 |
| ተበዳሪዎች | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ |
| አስፈፃሚ መ/ቤቶች | የፌዴራል የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር |
| የአካባቢ ዓይነት | [ ] A [ X] B [ ] C [ ] FI [ ] TBD (ወደፊት የሚወሰን) |
| ፕመሰ የተዘጋጀበት ቀን | የካቲት 10/1998 |
| ግምገማው እንዲደረግ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን | የካቲት 7/1998 |
| በቦርዱ የሚፀድቅበት ቀን | መጋቢት 14/1998 |

## 1. የአገሪቱና የዘርፉ ቅድመ ሁኔታ

ኢትዮጵያ በፖለቲካዊ እና በኢኮኖሚያዊ ረገድ መስቀለኛ በሆነ መንገድ ላይ የምትገኝ አገር ናት:: በግንቦት 1997 የተካሄዱትን ምርጫዎች ተከትሎ በአገሪቱ ውስጥ የተፈጠሩት የፖለቲካ ውጥረቶች እየተጠናከሩና በይበልጥ ይፋ እየሆኑ መጥተዋል:: በመልካም አስተዳደር ዘርፍ የተከሰቱት ከፍተኛ አደጋዎች ግልፅ እየሆኑ መጥተዋል:: በዚህም ምክንያት የተፈጠሩት የፖለቲካ ውጥረቶች በኢኮኖሚዉ አስተዳደር እና በጣም ጥልቅ በሆነው በልማቱ አጀንዳ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የማሳደር አቅም ያላቸው ናቸው:: የኢትዮጵያ የልማት አጋር መንግሥታት ይሰጥዋት የነበረውን የበጀት ድጋፍ ሰላገዱ ይኸም ደሃ-ደገፍ የሆኑትን ፖሊሲዎች በክልል ደረጃ ለማጠናከርና በወሳኝ የልማት፡ የአሰተዳደር፡ ለአደጋ የመጋለጥ፡ የአገልግሎት አቅርቦት፡ ባጠቃላይም በኤኮኖሚ ሥርዓትን በመሳሰሉት አርዕሰቶች ዙርያ መጠነ ሰፊ ውይይት ለማከሄድ መድረክ በመፍጠር ሲያገለግል ቆይቷል:: አጋር መንግሰታት ይህንን የወሰኑት መልካም አስተዳደርን በሚመለከቱ ተጨማሪ አደጋዎችን በማሰብ፡ በተለይም ቁጥጥር የሌለው የበጀት ድጋፍ በፖለቲካ ኃይሎች ሊጠለፍ ሰለሚችል፡ ወይንም ቅድሚያ ማግኘት የሚገባውን የመሠረታዊ አገልግሎት አቅርቦት አላማ ሊያሰት ይችላል ከሚል አሰተሳሰብ በመነሳት ነው:: በተጨማሪም በመልካም አስተዳደር ዘርፍ ግልፅ የሆኑ መሻሻሎች እስካልታዩ ድረስ፣ የእርዳታውን መጠን የማሳደግ ሃሳብ የለጋሾችን ድጋፍ እንደማያገኝ እሙን ነው:: መንግሥት የልማት ፖሊሲዎቹ ለፖለቲካ አመለካከቶች ተገዥ ሊሆኑ ይችላሉ የሚሉትን ማንኛቸውንም ታሳቢዎች ጨርሶ አይቀበልም:: እንዲያውም መንግሥት በከፍተኛ ኃላፊዎቹ አማካይነት ለድህነት ቅነሳ ፖሊሲና እና መላ ኢትዮጵያውያንን ለሚጠቅም መሠረተ ሰፊ እድገት ያለውን ቁርጠኝነት በድጋሜ አረጋግጧል::

የእርዳታውን መጠን በቅርቡ የመጨመሩ ጉዳይ ላልተወሰነ ጊዜ ቢተላለፍም ለጊዜው ግን መንግሥት፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች፣ ባንኩ እና የልማት አጋሮች በተጠናከረ የመልካም አስተዳደር አጀንዳ ዙሪያ በጋራ ተሰማምተው የሚሠሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፡ ባንኩ የ1998ን እና የ1999ን የበጀት ዓመት የሚሸፍን ጊዜያዊ አይሲኤኤስ አዘጋጅቷል::[1] በልማት ዕርዳታ ቡድን (ልዕቡ) ሥር የተደራጀው የብዙ ለጋሾች ጥረት አካል የሆነው የዚህ ጊዜያዊ ስትራቴጂ አጠቃላይ ግብ፣ መጠነ ሰፊ የሆነ የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም ለውጥ አፈፃፀምን መደገፍ እና በዜጐች እና በፖሊሲ አውጭዎች መካከል የስምምነት ጥረትን በማጠናከር በመላ አገሪቱ የሚታየውን ሥር-ሰደደ ድህነት ለመቀነስ ኢትዮጵያ የምታደርጋቸውን ጥረቶች ማጠናከር ነው:: በዚሁ መሠረት ባንኩ የአይሲኤኤስን ዝግጅት ለመምራት እንዲቻል በጥር ወር 1998 የመልካም አስተዳደር ሚሽን በኢትዮጵያ አሰማርቶ ነበር::

መሠረታዊ አገልግሎትን በማቅረቡ ረገድ ፍትሕአዊነት እና ግልፅነትን ማራመድ ጨምሮ፣ የባንኩ ተግባር በይበልጥ በመልካም አስተዳደር ላይ እንዲያተኩር በሚያስችል መልክ አይሲኤስ እንዲዘጋጅ ሚሽኑ የውሳኔ ሃሳብ አቅርቧል:: የመልካም አስተዳደር ሚሽኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የመንግሰት አወቃቀር ስርዓት ውሰጥ ለክልል በታች አስተዳደር መዋቅሮች በተለይ ለዞንና ለወረዳ የመዋለ ነዋይ ፈሰሰ በማድረግ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ማሰከበር እንዲችሉ መርዳትን በግልፅ ደግፏል:: ይህ ሲደረግ ግን በእርዳታው አጠቃቀም ላይ የተሻለ የክትትል እና የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት እንዲዘረጋ አሳስቧል:: የፖለቲካ ውጥረቶች በኢኮኖሚው አስተዳደር ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳያሰከትሉ ወይም አጠቃላይ የልማት ጥረቱን ወደኋላ እንዳይጐትቱት ጥንቃቄ ማድረጉ በእጅጉ አስፈላጊ ይሆናል:: በእርግጥም ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኢትዮጵያ ዘላቂ የልማት እና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራምን (ኤስዲፒአርዲፒ) ተግባራዊ በማድረጉ ረገድ የታየው ጥሩ የሥራ አፈፃፀም፡ በአገሪቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የታየው መልካም የሰብአዊ እድገት እና የኤኮኖሚ እድገት እንዲገታ ከተደረገ፡ ወይም እንዲቀለበስ ከተደረገ አለበለዚያም በፖለቲካዊ ጥቅም ከተጠለፈ አገሪቱ ብዙ የምታጣው ይኖራታል:: በመጨረሻም ድህነት ቅነሳን የሚያግዝና እድገትን የሚያፋጥን እንደ ህፃናት ክትባት እና ወባ ቁጥጥር የመሳሰሉ ከፍተኛ የሆኑ አዎ-ንታዊ ተፅእኖ ሊኖራቸው የሚችሉ ተግባራት እንዳይታለፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ግልፅ የሆኑ እድሎች አሉ::

*የሰብዓዊ መብቶች መሻሻል::* ኤስዲፒአርፒ ተግባራዊ በመደረጉ፡ በተለይ በሰው ኃይል ልማት አመልካቾች (ሰንጠረዥ 1)፣ በትራንስፖርት፣ በኢንቨስትመንት ሁኔታ፣ በአነስተኛ ከተሞች ማበብና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከሚደረገው ተጋድሎ አንፃር አይነተኛ ውጤቶችን ማሰመዝገብ ተችሏል:: ለድህነት ቅነሳ የሚደረገው ወጪ ድርሻ በ1991-1992 ከበጀቱ 39% የነበረው በ1997-1998 የበጀት ዓመት ወደ 54% አድጓል:: ኢትዮጵያ የሲቪል ሰርቪሱን የስራ አፈፃፀም ለማሻሻል አገር በቀል የሆኑ ፕሮግራሞችን ነድፋ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች:: በሌላ በኩል ያልተማከለው የአስተዳደር ስርዓትዋ ጥልቀት እንዲኖረው በተሻሻለ የገንዘብ ቁጥጥር ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ትገኛለች:: በቅርቡ የሚወጣው፣ በእድገት እና በመልካም አስተዳደር ላይ የተመሰረተው የዓለም ባንክ አገራዊ የኢኮኖሚያዊ ማስታወሻ 1998 (አኤማ) ባለፈው አስርት ዓመታት ዓይነተኛ እድገት መመዝገቡን አሳይቷል:: ይህ ጥሩ እድገት ሊገኝ የቻለው የክልልና የአካባቢ ተቋዋማት ባሳዩት መሻሻልና ያገልግሎት አቅርቦትና የመሠረተ ልማት ተግባራቶቻቸው መጎልበት ነው::

**ሰንጠረዥ 1፡ በ1987/88 -1996/97 የተመረጡ የሰብአዊ መብት ዕድገት አመልካች እንቅስቃሴችና በድህነት ቅነሳ ዘርፎች ላይ የተደረጉ ወጪችን የሚያሳይ ሠንጠረጅ**

| ዘርፍ | አመልካች | ዓመት | | | | ለውጥ በመቶኛ 1996/1988 | ለውጥ በመቶኛ 1996/1992 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1987 1988 | 1989 /1990 | 1991/ 1992 | 1996/ 1997 | | |
| ትምህርት | አንደኛ ደረጃ (1-6) አጠቃላይ የተማሪች ምዝገባ %<br>የመሰረተ ትምህርት ምዝገባ በ% | 37.4<br>25.8 | 52.3<br>26.6 | 61.1<br>29.2 | 74.2<br>37.9 | 98.4<br>46.9 | 21.4<br>29.8 |
| ጤና | ከ5 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ህፃናት ክትባት<br>ፈንጣጣ<br>ቢሲጂ | 39.1<br>40.1 | 46.9<br>50.9 | 48.1<br>49.1 | 56.8<br>54.9 | 45.3<br>49.6 | 18.1<br>14.4 |
| ውሃ | ጤናማ የሆነ የመጠጥ ውሃ የማግኘት እድል በመቶኛ | 19.1 | 23.7 | 27.9 | 35.9 | 88.0 | 28.7 |
| የድህነት ዘርፎች | ዘርፎቹ ላይ የሚደረገው ወጪ በድህነት ዘርፎች ላይ የሚደረገው የወጪ ክፍልፋይ ከጠቅላላው ወጪ መቶኛ | | 36.7 | 26.4[2] | 54.2 | | |

ማስታወሻ፡ [1] በመንግሥት እንደተገለፀው ዘርፎቹ ትምህርት፣ ጤና፣ ግብርና የተፈጥሮ ሀብት እና የገጠር መንገድ ዘርፎች ናቸው::

[2] ይህ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መሃከል ጦርነት የተካሄደበት ዓመት ነበር::

*ምንጭ፣ ኤስዲፒአርፒ ኤፒአር 2 እ.ኤ.አ ሐምሌ 2005 ሞፌድ እና የአለም ባንክ የስራ ባልደረቦች ግምት*

[1] *በዚህ ሰነድ በሌላ መልኩ ካልተገለፀ በስተቀር «የበጀት አመት» የሚለው የሚጠቀሰው የአለም ባንክን የበጀት አመት ነው:: አሁን ያለው የዓለም ባንክ የበጀት አመት ማለትም 1997-1998(ኤፍዋይ06) ከ1997-1998 የኢትዮጵያ የበጀት አመት (ኢኤፍዋይ 98) ጋር ተመሳሳይ ነው:: ይሁን እና የኢትዮጵያ የበጀት አመት የሚቆየው ከሐምሌ 1 ጀምሮ እስከሚቀጥለው አመት ሰኔ 30 ድረስ ሲሆን፣ የአለም ባንክ የበጀት አመት ደግሞ የሚቆየው በየአመቱ ከሰኔ 24 እስከ ሚቀጥለው አመት ሰኔ 23 ድረስ ነው::*

እነዚህ ግኝቶች ኢትዮጵያ ማንኛቸውንም የምዕተ ዓመት ግቦች ተግባራዊ ለማድረግ ያላትን እድል በዘላቂነት ለመቀጠል ከሚያስችላት ጥልቀት ካለው የልማት ስትራቴጂ የመጀመሪያዎቹን እርምጃዎች የሚወክሉ ናቸው:: የአኤማ ማስታወሻ እንደሚያመለክተው በመልካም አስተዳደር መስክ የማያቋርጥ እድገት ማስመዝገብ የሚቻለው: ድሀ-ደገፍ ተቋማትን በማጎልበት እና ዜጐችን የስልጣን ባለቤት ማድረጉ ችግር አብዮቹ ለዕድገት ማነቆ ሊሆኑ ከሚችሉት ጥቂቶቹ ናቸው::

## 2. ግቦች

የመአፕ እንቅስቃሴ የፕሮጀክት ልማት ግብ ከክልል በታች ያሉ አስተዳደሮች የሚሰጡትን አገልግሎቶች እየተንከባከቡ፡ በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ያለው ግልፅነት እና ተጠያቂነት ሥር እንዲሰድና እንዲጎለብት ማድረግ ነው:: የታቀደው የመሰረታዊ አገልግሎቶች መንከባከብ ፕሮጀክት (መአመ) ዓላማ ኢትዮጵያ በሰው ኃይል ልማት ረገድ የምዕተ ዓመቱን ግቦች ለሚሟላት የምታደርገውን እንቅስቃሴ መደገፍ ብቻ ሳይሆን በጤና፣ በትምህርት እና በውሃ ዘርፍ ለሚደረጉ መሰረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት የሚውለው ንብረት ዝቅ እንደማይል ለማረጋገጥና: በኢትዮጵያ የአጭር ጊዜ ወጪ እና የፋይናንስ ማእቀፍ (ኤምኢኤፍኤፍ) እንደተመለከተው እድገቷ እንዲቀጥል ለማድረግ ሲሆን: እንዲያውም በአንዳንድ ዘርፎች (እንደ ክትባት፣ የቤተሰብ እቅድ እና የወባ ቁጥጥር) ባሉት ዕድገቷ እንዲፋጠን ማድረግንም ይጨምራል:: ፕሮግራሙ፣ በክልል ደረጃ የሚቀርቡት መሰረታዊ አገልግሎቶች ባሉበት እንዲቀጥሉ ይሻል:: በኢትዮጵያ ያልተማከለ የአስተዳደር ስርዓት አብዛኛቹ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ አገልግሎቶች የሚሰጡትና ወጪያቸው የሚሸፈነው ከክልል መለስ በሆኑ አሰተዳደሮች ሰለሆነ ዕቅዱ እነዚህን መሠረታዊ አገልግሎቶች ባሉበት መንከባከብ ይፈልጋል::

ለመአመ ሲባል መሰረታዊ አገልግሎቶች የሚለው ከዚህ የሚከተለውን ሰፊ ትርጉም የሚያካትት ነው: እሱም *ለድህነት ቅነሳ በቀጥታ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ በክልል ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ወይም ማኅበራዊ ተፅእኖ ያላቸውን* (የ1ኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ ጤና፣ የውሃ አቅርቦት እና የጽዳት፣ የገጠር መንገድ፣ የግብርና ኤክስቴንሽን፣ ሥራ፣ ማኅበራዊ ደህንነትን)፣ *እንዲሁም በኢኮኖሚ እድገት ላይ ባላቸው ተፅእኖ ምክንያት ለድህነት ቅነሳ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ አገልግሎቶችንና፣ በመሰረታዊ የአስተዳደር አገልግሎት ላይ የሚደረግ ወጪን ... ወዘተ ሲሆን* ካለነዚህ ወጪዎች በጀት ሊዘጋጅ ወይም ሊፀድቅ አይችልም: ክፍያዎች ሊፈፀሙ አይችሉም፣ ሂሳቦችም ሊያዙ አይችሉም ...ወዘተ፤ በመሆኑም አገሪቱ ለዜጐቿ ያላት ተጠያቂነት እንዲሻሻል ከተፈለገ እነዚህ ወጪዎች ወሳኝነት ይኖራቸዋል::

ይህ አተረጓጎም ለሕዝብ ፀጥታ እና ደህንነት የሚደረጉ እና እንደዚሁም ከድህነት ቅነሳ ጋር ያላቸው ቁርኝት አጠያያቂ በመሆኑ በአንዳንድ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ የሚደረጉ ወጪዎችን አያካትትም (ለምሳሌ፣ ማዕድን እና ኢነርጂ እና «ልዩ ልዩ ወጪዎች»):: በመአመ ስር የተመረጠው የአሰራር ዘዴ፣ ከፍ ብሎ በተሰጠው ትርጉም መሠረት: የፕሮጀክቱ ፋይናንስ መቼም ለተፈላጊ ድሃ-ጠቀም አንቅስቃሴዎች የክልል መለስ አሰተዳደሩ ከሚያደረገው ወጪ(ደህንነት ነክ ያልሆኑ ወጪዎች) መብለጥ እንደሌለበት ነዉ የሚያመለክተዉ:: ገንዘቡ ስምምነት በተደረገባቸው የዘርፍ ስትራቴጂዎች፣ ማለትም በትምህርት፣ ጤና፣ ውሃ እና ጽዳት... ወዘተ አፈፃፀም ላይ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ይጠበቃል:: መአመ በበታች አስተዳደር ደረጃ በሚደረጉ የፖሊሲ ምርጫዎች ላይ ተፅእኖ ማድረግ የሚያስችል የራሱ ቀጥተኛ የሆነ የአሠራር ስልት ባይኖረውም ቅሉ ለመሠረታዊ አገልግሎቶች የሚደረገው የገንዘብ ፈሰስ እንዲቀጥል ማድረጉ የአገልግሎት ሽፋኑ እንዲጨምርና እንደዚሁም ጥራቱም እንዲሻሻል ያደርጋል::

ከዚህ በተጨማሪ በአዲስ መልክ የቀረበው የጤና ድጋፍ ገንዘብ በክትባት መጠን፣ በወባ የአልጋ መረብ አጠቃቀም መጠን፣ በወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም መጠን፣ ፋይዳ ያላቸው መሻሻሎች እንዲመዘገቡ ማድረግ ይኖርበታል።
ይህም ከወዲሁ ከሞት በሚተርፉ የህፃናት እና እናቶች መጠን ላይ በጐ ተፅእኖ እንደሚኖረው ይጠበቃል። እነዚህ ከፍተኛ ግቦች እሰተ ምን ድረሰ ተግባራዊ መሆናቸውን ማወቅ የሚቻለው በአሃዝና በጥራት የአገልግሎት አቅርቦቱን በሚዳሰሳ ቅንቀና አማካይነት ነው።

ቀደም ሲል ከነበሩት የበጀት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር፣ በ1997/98 የበጀት ዓመት የፐልአ ውጤት የሚለካው ከክልል በታች ባሉ መዋቅሮች የተሻሻለ መሰረታዊ አገልግሎት አቅርቦት ከመኖሩ አንፃር ሲሆን፡ በተጨማሪም በ1999 የበጀት ዓመት በመሠረታዊ አገልግሎት አቅርቦት ረገድ ተጨማሪ እድገት ይጠበቃል። በጤና አገልግሎት ዘርፍ የሚደረጉ መሻሻሎች የሚገመገሙት ፌዴራል መንግሥት ለክልል ባለስልጣናት የሚሰጡትን ወሳኝ የሆኑ የጤና አቅርቦቶች ከቁጥር በማስገባት ነው።

ፐልአ የሚገመገመው በክልል መለሰ አሰተዳደሮች ወጪዎች ላይ ጥብቅ የሆነ የገንዘብ ቁጥጥርና ዘገባ አማካይነት ሲሆን፡ በተጨማሪም የዜጐችን ምርጫዎች ከአካባቢ አስተዳደር ባለስልጣናት ውሳኔዎች ጋር በተሻለ ሁኔታ ለማጣመር አዳዲስ የተጠያቂነት ስርዓቶችን በመዘርጋት ይሆናል።

**3. የባንኩ ተሳትፎ አስፈላጊነት**

ቀጥተኛ የበጀት ድጋፍ በሌለበት ሁኔታ፡ ጊዜያዊ ስትራቴጂዉ፡ ድሆች ለአያሌ ትውልድ ስር ሰዶ ከቆየ የድህነት ወጥመድ ለመላቀቅ ለሚያደርጉት ትግል፡ ባንኩ የሚሰጠውን የመሠረታዊ አገልግሎት ወሳኝ ድጋፍ እንዳያቋርጥ ይመክራል። በተመሳሳይ ሁኔታ ባንኩ ከሌሎች ለጋሽ አጋሮች ጋር በመሆን መንግሥት እነዚህን አገልግሎቶች ፍትሐዊ፣ ግልፅና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲያቀርብ ለማገዝ የሚደረጉትን ጥረቶች በይበልጥ እያጎለበተ፡ ተቋማዊ ንብረቶችን በመንከባከብ አመቺ ሁኔታ ሲፈጠር እርዳታው የሚፋጠንበትን ምንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል።

ለድሀ-ደገፍ ዘርፎች የተመደበውን የመንግሰት በጄት ከቁጥር በማስገባትና ከፍ ብለን ያየነውን የፋይናንስ ክፍተት ሰንመለከት፡ የመንግሥት ወጪ ለ1998 ከተመደበው በጀት በታች ከወረደ በኢትዮጵያ ድሆች ላይ ሊይሰከትል የሚችለው እንድምታ ግልፅ ነው። በዚህ ምክንያት የአለም ባንክ እና ሌሎችም ዓለምአቀፍ የልማት አጋሮች (ዲኤፍአይዲ፣ ሲዳ) በአጭር ጊዜ ውስጥ ለቀጥተኛ በጀት ድጋፍ አማራጭ የሚሆን እንቅስቃሴ በፍጥነት ማዘጋጀት የጀመሩት። ይህ አማራጭም የሚያተኩረው በመሰረታዊ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ሲሆን፣ እሱንም በኢትዮጵያ የሚያንቀሳቅሱት በአመዛኙ የክልል በታች መንግሥታዊ መዋቅሮች ናቸዉ።

*የታቀደው የመአመ ፕሮጀክት ዓላማ መንግሥት፡ በተለይም ለክልል መለሰ አሰተዳደር፡ የሚያደርገውን ድሃ ደገፍ ወጪ እንዳይቀንስ ለማድረግ ማንኛውንም ድጋፍ መሰጠት ነው። የመአመ አሰራር የሚጠቀመው በመንግሥት የገንዘብ አስተዳደር ስርዓት እና የአገልግሎት አቅርቦት መዋቅሮች ነው። የመአመ የአሰራር ዘዴ ቀደም ሲል ከነበረው የቀጥተኛ በጀት ድጋፍ ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር የንብረት አጠቃቀምን በተመለከተ ይበልጥ ወቅታዊና ዝርዝር ዘገባ በመጠየቁ፡ ግልጽ ክትትልና እንደዚሁም የገንዘብ ፈሰቱን ፍትሐዊነት በመቆጣጠሩ፡ ከክልል ደረጃ ይልቅ በክልል በታች አሰተዳደሮች የአገልግሎት አቅርቦት ውጤቶችን በመከታተሉ፡ እንዲሁም መንግሥት የመሠረታዊ አገልግሎት አቅርቦትን ለማጠናከር ፈሰሰ ለማድረግ የገባውን ቃል ለመደገፍ የአካባቢ ተጠያቂነትን ለማበረታታት አዳዲስ ዘዴዎችን በማስተዋወቁ ነው።*

*መአመ እንደዚሁ መንግሥትና ዜጐች የሚያከብሩት የተጠያቂነት ስርዓቶችን ይገነባል፡ እነዚህም ስርዓቶች በአይሲኤስ እና ከዚያም ወዲያ ባለው ጊዜ በይበልጥ ይጠናከራሉ።*

በዚሁ መሰረት ግዚያዊ ስትራቴጂው ይህንን አሰራር የሚያየው የባንኩ ያሁንና የወደፊት ያልተማከለ አገልግሎት አቅርቦት የሚደግፉ ዕቅዶች የሚያልሙበት የተቀናጀ አውታር ለመፍጠር የሚያገለግል አብይ መድረክ ሲሆን፡ ይህም መድረክ ባልተማከለ ዉሳኔ አሰጣጥና በአቅም ማጎልበት ሂደት ላይ በማተኮር ገንዘቡ ድሆች ቅድሚያ ለሚሰጡት ጉዳይ እንዲዉል ለማድረግ ይጥራል፡፡

የዚህ የተቀናጀ አዉታር አይነተኛ ባህርያት፡ (ሀ) በክልል ደረጃ የተደረገው የንብረት ፍሰት እንዴት እንደተካሄደ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ለመፍጠር ሕዝብን ያሳተፈ የክልል ግልጽ ግምገማ ማካሄድ (ለ) በዜጐች ተወካይ ቡድኖች እና ዜጐች ዘንድ፣ የበጀት አመዳደብ እና የወጪ ሂደቶችን በተመለከተ የተጠናከረ ግንዛቤ እና ተሳትፎ (የወረዳ እና የቀበሌ ምክር ቤቶች፣ የሲቪል ማህበርሰብ ድርጅቶች) እንዲኖራቸው ማድረግ፣ (ሐ) ከፌዴራል አንስቶ ወረዳ ደረጃ ድረስ በዓይነት የተደረጉ ሰጦታዎችን ስምምነት ለተደረሰባቸው ድሃ-ደገፍ ተግባራት ማድረስ፡ (መ) የመንግሥትን የሥራ አፈፃፀምና እንደዚሁም ወደ ዕቅድ መመለስ አሠራር መገምገም የሚያሰችል መሠረተ ሰፊ የዜጎችን የክትትል ችሎታ የሚያዳብር የተለያየ የግምገማና የክትትል ፕሮግራም ማውጣት (የወረዳ መነሻ አሃዞችን፣ የዜጐችን አመለካከት የሚያንጸባርቁ ቅንቀናዎችንና፣ ዜጐች የሚያደርጉትን የዘገባ ካርዶችን ማቀናጀት) (ሠ) ተስማሚ የሆነ ቀጥተኛ የድጋፍ ስርዓት (በብዙ ለጋሾች ድጋፍ የተቋቋመው) የሲቪል ማኀበረሰቡ በፖሊሲ እና በመንግሥት በጀት አወጣጥ ላይ የተጠናከረ ተሳትፎ እንዲኖረው የሚያደርግና (ረ) በመንግሥት የሚመደበው በጀት በአካባቢ የፖለቲካ ኃይሎች ቋሚ ተጠቃሚች እንዳይጠለፍ ለመከላከል የውስጥ እና የውጭ የተጠያቂነት ስርዓቶችን መዘርጋትን ያጠቃልላል፡፡

ቀደም ሲል የቀጥተኛ የበጀት ድጋፍ ሲያደርጉ የነበሩት ባንኩና ሌሎቹ ለጋሾች በእነዚህ ችግሮች አንጻር በፖሊሲ ደረጃ በመንግሥት ላይ በጐ ተፅእኖ ለማሳረፍ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ ከፍላጐት ጋር ተመጣጣኝነት ያለው ገንዘብ እንዲገኝ ለሚደረገው ጥረት፡ በባንኩ ሞያና ችሎታ በመጠቀም መንግሥትን፡ የሲቪል ማህበረሰቡንና ለጋሾችን፡ ውጤታማ የሆነ የአገልግሎት አቅርቦትና የተሻሻለ ተጠያቂነት እንዲኖር በሚሻ የጋራ ራዕይ ላይ እንዲየተኩሩ በማድረጉ ረገድ የባንኩ ቁርጠኝነት መኖር በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

የታቀደው አሰራር ዘዴ በዳግ (የኢትዮጵያ ዋና ዋና የልማት አጋሮች ቡድን) ሰምምነት መሠረት የተቀረጸ ሲሆን ኢትዮጵያ ለመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት እንድትሰጥ የሚጠይቅና፡ ይህም ሲደረግ በከፍተኛ ጥረት የተገኙት የልማት ውጤቶች እንዳይፈርሱ ወይም እንዳይቀለበሱ የማድረጉንም አስፈላጊነት ያካትታል፡፡

**4. መግለጫ**

**ማጠቃለያ፡** የዚህ ፕሮጀክት አራቱ ክፍሎች ፐልአን በቀጥታ የሚደግፉ ናቸው፡፡ እያንዳንዱን ክፍል በመቅረጹና በመገምገሙ ረገድ አራት የተለያዩ መርሆች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

- መንግስት መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለማጠናከር ካለው ቁርጠኝነት አንፃር ፕሮጀክቱ በእያንዳንዱ ዓመት መንግሥት ለዚህ አላማ የሚመደብ ለክልል በታች አሰተዳደሮች የሚደርሰ ተጨማሪ ገንዘብ በባጀት መያዙን እንዲያረጋግጥ ይጠይቃል፡፡
- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለተከሰቱት ሁኔታዎች ምላሽ ለመስጠት ለጋሾች፡ የዓለም ባንክን ጨምሮ፡ ወጪዎችን መከታተልና የተለዩ የመንግስት ፈሰሶችን መገምገም የሚያሰችል የብድር መሣርያ በመፍጠር፡ ድሆች ወሳኝ የሆኑ አገልግሎቶችን ያለማቋረጥ የሚያገኙበትን ለማረጋገጥና ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚያራምደው የፖለቲካ አመለካከት ምንም ይሁን ምን፡ ፍትሃዊ በሆነ ምንገድ የመሰረታዊ አገልግሎት ድርሻውን ማግኘቱን ለማረጋገጥ ሲሹ ነበር፡፡ በመሆኑም ይህ ፕሮጄክት እነዚህን ሁለት ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ በሁለት ሌላ መርሆች ይጠቀማል፡፡ በመጀመሪያ የሂሳብ ሃላፊነት የሚገመገመው ሰለ ገቢና ወጪ በሚቀርብ መጠነ ሰፊና መደበኛ ዘገባ ይሆናል፡፡ ይኸው ዘገባ ለጋሹ የመጀመርያውን ክፍያ ልዩ ሂሳቡ ውሰጥ ከማሰገባቱ በፊት አንደ ክፍያ ቅድመ ሁኔታነት ሲጠቀምበት፡ የድጎማውን ልዩ ሂሳብ ሳጥን ለመተካት በሚፈለግበት ወቅትም እንደ ወጪ ማጣርያ ሰነድም ያገለግላል፡፡

የገንዘብ አጠቃቀሙን በሚመለከት ከሚፈለገው ከፍተኛ ክትትልና የሂሳብ ኦዲት በተጨማሪ በመንግስት የባጀት ስርአት ያሉት ሁሉም ደንቦች በሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ የተለየ ግልጽ ግምገማ ይደረጋል:: እንደዚሁም ሁሉም ወገኖች ክልሎች ወረዳና የከተማ አስተዳደሮች በህገ መንግስቱና በባጀት አንቀጾች መሠረት የተወሰነውን ተገቢ ድርሻቸውን መቀበላቸውን ማረጋገጡ አስፈላጊ ይሆናል::

- ሁለት ክፍሎች (ሰንጠረዥ3ና 4ን ከዚህ በታች ይመልከቱ) በክልል ደረጃ የሚገኙ የመንግስት የፋይናንስ ስርአቶች አዲስ የተጠያቂነት አሠራርን ለማስተዋወቅ የሚያስችል ፕሮግራምን ይደግፋሉ:: ማለትም በመንግስት በኩል ያሠራር ጥራትና ግልጽነት ተፈላጊ በመሆኑና እንደዚሁም በሕዝቡ በኩል የተጠናከረ ተሳትፎ ወሳኝ በመሆኑ ፕሮጀክቱ የሚያስመዘግበው ውጤት የሚመዘነው በነዚህ መሰኮች በተጠያቂነት አንጻር በተደረጉ ጥረቶች ስኬት ነው::

**ፕሮጀክቱ አራት ክፍሎች ይኖሩታል::**

**ክፍል አንድ መሰረታዊ የአገልግሎት ድጎማ**: በክልልና በአካባቢ አስተዳደሮች የሚቀርቡ መሰረታዊ አገልግሎቶች መቅረባቸውን ማረጋገጥ::

ይህም የሚያካትተው:
(ሀ) የድጎማ ባጀትን ለክልል መንግስታት መስጠት የክልል መንግስታት በበኩላቸው ለራሳቸው መሰተዳደሮች የባጀት ፈሰስ ማድረግ:
(1) ተጨማሪ ኢላማች ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ለመሠረታዊ አገልግሎቶች የሚሰጠው ድጎማ መጠንና ወቅታዊነትን
(2) የክፍፍል ደንቦቹን ፍትሐዊ በሆነ መልክ ተግባራዊ ማድረግ (3) ለመሠረታዊ አገልግሎት የተደረገ የወጪ መጠንና ክፍፍሉ::
የዚህ ክትትል ውጤት በክፍያ ቅድመ ሁኔታነት ይወሰዳል:

ፍትሀዊነትንና የፖለቲካ መረጋጋትን ለማረጋገጥ የፌደራል አብዛኛው ገንዘብ ለክልሎች የሚፈሰው በፌደራሉ የድጎማ ስርአት አማካኝነት ይሆናል:: የባጀት ድጎማ ዝውውር የሚደረገው በፌደራሉ ፓርላማ ሁለተኛ ምክር ቤት ማለትም በፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚጸድቀው ቀመር መሠረት ነው:: የሕዝብ ብዛትን፣ የልማት ክፍተትን፣ የገቢ አቅምን የሚያጣምረው ይኸው ቀምር ከ1995/96 የበጀት አመት ጀምሮ ስራ ላይ ውሎ ይገኛል:: የፌዴራሉ የድጎማ ስርአት የተመሠረተበት መርህ በክልሎች መካከል ያለውን ልዩነት ለመቀነስ ወይም ያለዉን ሃብት በክልሎች መካከል በእኩል ደረጃ መከፋፈልን የሚሻ ነው:: በዚሁ መሰረት የራሱ ጠንካራ የገቢ ምንጭ ያለው አዲስ አበባ ከተማ፣ ከማንኛቸውም ክልል የላቀ ገቢ ሰላለው: በባጀት ድጎማ መልክ ምንም ድጋፍ ከመንግስት ግምጃ ቤት አያገኝም::

**ክፍል 2 የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ**
በክፍል 1 በተመለከተው የተያያዘ-ድጎማ በወረዳ ደረጃ ፈሰስ ማግኘት ከሚችሉት ውጭ ለመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ወሳኝ የሆኑትን ግብአቶች ለመሸፈን የተዘጋጁ የተሰባሰቡ ድጎማዎች: ይህ ፕሮግራም የሚያተኩረው በተለይ በወባ ቁጥጥር ላይ ሲሆን ባንኩ በኢትዮጵያ ለሚመራው የወባ ቁጥጥር ማጠናከሪያ ፕሮግራም እንደመጀመርያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል:: ፕሮግራሙ አራት ዓይነት ተግባራትን ይደግፋል::

(1) _ሸቀጦች_: እንደ ቫክሲኖች: የወሊድ መቆጣጠሪያ: ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ ጸረ-ተባይ የተረጨባቸው የወባ መከላከያ መረቦች: የወባ መድሀኒቶች፣ ጸረ ተባዮች: የመርጫ መሳሪያ-ዎችና ሌሎች በነጻ የሚሰጡ ሸቀጦች... ወዘተ ሲሆኑ: የጤናውን ልማት ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ አይነተኛ ግብአት የሆኑትን በዓለም አቀፍ ገበያ ለመግዛት እንዲቻል አስፈላጊውን የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ:: ከዚህ በተጨማሪም የጤናው ዘርፍ ልማት አካል የሆኑ ሌሎች ሸቀጦችን በነጻ ማቅረብ:

(2) _የአቅም ግንባታ_: የሰው ኃይል ልማትን ያካተቱ ተግባራትን: የቴክኒክ እገዛን: ክትትልና ግምገማን: እንዲሁም ኦፕሬሽናል ምርምርንና በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ደረጃ የሚከናወኑ ሌሎች ተግባራትን ሲመለከት፣

(3) *<u>ግዥንና ሎጅስቲክን ማጠናከር</u>*፡ ይህም የሚያካትተው ስልጠናንና የዓለም አቀፍ ግዥ ቲኤን፣ ማእከላዊ የህክምና መጋዘንና የብሔራዊ ስርጭት ስርዓትን ማጠናከር እና
(4) *<u>አስቸኳይ የጤና ፍላጎቶች</u>*፡ ይህም የሚያካትተው ለአደጋ ጊዜ ዝግጁነት የሚያስፈልጉ ክትባቶችና መድሃኒት ክምችትን ነው፡፡

**ክፍል 3 በመንግሥት አሰራር ላይ የሂሳብ ግልጽነትና ተጠያቂነትን** በከፍተኛ ደረጃ ለማጎልበት ይቻል ዘንድ በክልል በወረዳና ዝቅተኛ አስተዳደር ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራትን የሚደግፍ ሲሆን፡ (የባጀት ዝግጅት ወጪና ኦዲት) ከዚህ በተጨማሪም ሰፊ ተሳትፎን የዜጎች ተወካይ ቡድኖች ስልጣንና እንደዚሁም ዜጎች በመንግስት የባጀት ሂደቶችና በመንግስት አገልግሎት ላይ በይበልጥ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስቻል፡፡ ይህ ክፍል ገኤልሚ የራሱን አቅም ለማጎልበት እና ለክልሎችና ለወረዳዎች ቲኤዎችን ለመስጠት እንዲችል የሚቀጥራቸውን የሂሳብ ባለሙያዎች ወጪ የሚሸፍን ይሆናል፡፡ እንደዚሁም ፕሮግራሙ በፌዴራል ኦዲተር ጄኔራል መሥሪያ ቤት ደረጃ መከናወን የሚገባቸውን አፋጣኝ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ወጪ የሚሸፍን ይሆናል፡፡

**ክፍል 4 ማህበራዊ ተጠያቂነት**፣ ይህ ፕሮግራም የተነደፈው በአያሌ ለጋሾች ድጎማ አማካኝነት ሲሆን ተግባራዊ የሚደረገውም በዓለም ባንክ አማካኝነት ነው፡ ባልተማከለ የአገልግሎት አቅርቦት ውስጥ የዜጐችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖችን ድምጽ ለማጠናከር እንዲቻል የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፡ እንዲሁም የሙከራ ተግባራትን ያከናውናል፡ ከዚህ በተጨማሪም ዜጐች በመንግሥት የበጀት ዝግጅት ሂደቶች ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ያካሄዳል፡፡ በመጨረሻም መታወቅ የሚገባው ጉዳይ የመአመ የአሰራር ዘዴ የተዘጋጀው ደካማ አስተዳደር ላለበት አካባቢ ሲሆን፡ የዚሁ የመአመ አላማ ድሆች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማገዝ እና እንደዚሁም ገንዘቡ የታቀደለትን ዓላማ የሚጠቅም መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ የመአመ መነሻ ሃሳብ ከዚህ የሚከተለው ነው፡፡ ለድሀ ሕዝቦች ማኅበራዊ ደህንነት የታቀዱ ወሳኝ የሆኑ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች በየጊዜው ከሚቆም እና ከሚቀጥል የእርዳታ ሂደት መጠበቅ ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ሰለዚህም መአመ በቅድሚያ የተዘጋጀ የተጠናከረ የአሰራር እና የተጠያቂነት ስርዓቶች ያሉት ሲሆን፣ እነዚህም ስርዓቶች አገልግሎቶቹ ለታሰቡት ተጠቃሚዎች የሚዳረሱ መሆናቸውን ለልማት አጋሮች ማረጋገጥ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረትም ፕሮግራሙ መቀጠል የሚኖርበት መሆኑን የሚያሰረግጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁንና ምናልባት የመአመ አጋሮች በየጊዜው በሚደረጉት ግምገማች የአገልግሎቶቹ ፍትሐዊነት ጥያቄ ውስጥ ወድቋል ወይም ውጤታማ አይደለም ወይም ተጠያቂነት የለውም የሚል ዘገባ ከደርሳቸው የመአመ ገንዘብ እንዲቀነስ ወይም እንዲታገድ ሊወሰኑ ይችላሉ፡ ይህንንም ማለት የፕሮጀክቱ የልማት ግቦች ተግባራዊ አልሆኑም ማለት ነው፡፡

## 5. የፕሮግራሙ የገንዘብ ሽፋን

| ምንጭ | የአሜሪካ ዶላር በሚሊዩን |
|---|---|
| ተበዳሪ/ተጠቃሚ | 1,727.00 |
| ዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር | 255.00 |
| ኢንግላንድ: የእንግሊዝ የአለም አቀፍ ልማት መምሪያ (ዲኤፍአይዲ) | 191.00 |
| የካናዳ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (ሲዳ) | 21.00 |
| የአየርላንድ የልማት ትብብር (ዲሲአይ) | 1.00 |
| ድምር | 2,195.00 |

## 6. የትብብር ሁኔታዎች

ክፍል 4 ለማስፈጸም የተዘጋጀው የሶሻል ተጠያቂነት የአጋሮች ትብብር ስምምነት በዝግጅት ላይ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የታቀዱት ተግባራት ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ የሲቪል ማህበረሰብ ቋሚ ትብብር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህ ክፍል በበኩሉ መአመ በከፍተኛ ደረጃ ለማቀናበር የሚሻውን ያገልግሎት አቅርቦትና በመንግስት የገንዘብ ፈሰሰ ስርዓት ውስጥ የሚያልፈውን ንብረት የማቀናበር ጥረት ወሳኝ አካል እንደመሆኑ መጠን፡ ይህ ትብብር ለመአመ ውጤታማነት በአጠቃላይ ወሳኝ ነው፡፡

## 7. አፈፃፀም

መአመ ተግባራዊ የሚሆነው በሁለት ዓመት ጊዜ ሲሆን፡ በነባሩ የመንግሥት መዋቅር በመጠቀምም ነው:: የተቋማዊ እና የአፈፃፀም ዝግጅቶቹም እንደሚከተለው ነው::

### የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

(1) በፌዴራል ደረጃ *የፌዴራል ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር* አስፈፃሚ ድርጅት ለክፍል 1 እና 3 ኃላፊ ይሆናል:: በእነዚህ ክፍሎች ዙሪያ ለሚከናወኑ የፕሮጀክት ተግባራት አጠቃላይ አመራር መስጠት ማቀናጀት፣ ማስተባበር፡ ክትትል ማድረግና መገምገም የፌገኤልሚ ሙሉ ኃላፊነት ነዉ:: እንደ አስፈላጊነቱ ለቴክኒክ እገዛ አግባብነት ካላቸው የዘርፍ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እና የልማት አጋሮች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል:: የፌገኤልማ ኃላፊነት የሚከተሉትን ያካትታል፡ (ሀ) ለመሰረታዊ አገልግሎት ለክልል መንግሥታት የሚደረጉ የድጐማ ገንዘቦችን ስምምነት በተደረሰባቸው የገንዘብ ዝውውር ቀመሮች አማካይነት በወቅቱ እንዲዛወር ማድረግ፣ ውጤታማ የሆነ የገንዘብ አስተዳደር መኖሩንና የቁጥጥር መስፈርቶች ተፈፃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ (ለ) የተለያዩ የቴክኒክ እርዳታዎችን አፈጻጸምና ስርዓት የሚፈጥሩ ተግባራትን በመምራት የበጀት አፈፃፀምን ግልጽነትና የተጠናከረ የወጪ ዘገባ አቃራረብን በማረጋገጥ፣ የመሠረታዊ አገልግሎቶችን አቅርቦት ዋና ውጤቶች ለመከታተል የሚደረገውን ጥረት ማሻሻል (ሐ) የመንግሥት ወጪዎችን የገንዘብ አወጣጥ ግልፅነትንና ማኀበራዊ ተጠያቂነትን ማሻሻልና በክልልና በአካባቢ አስተዳደር እንዲሁም በአግልግሎት መስጫ ተቋማት ደረጃ መሰረታዊ የአገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ማድረግ::

(2) በክልል ደረጃ *የክልል የፋይናንስ እና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች* (ፋኤልቢ) (ለፕሮጀክት አፈፃፀም ቅንጅት እና ለፕሮግራሞች መጀመር፣ እንደአስፈላጊነቱ ከሌሎች የመስመር መስሪያ ቤቶች የሚገኝን የቴክኒክ እገዛ ማቀናጀት፣ ከአካባቢ አስተዳደር የሚቀርቡ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርቶችን መገምገምና ማጠናከረ፣ ለአስፈፃሚ ኣካላት አስተያየት ማቅረብና ለአጠቃላይ የሥራ አፈፃፀምና ለሃብት አጠቃቀም ክትትል እንዲሁም ግምገማ ኃላፊ ይሆናሉ:: ለመሰረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት አስቀድሞ በተዘጋጁ እቅዶች መሰረት ፋኤልቢ ለአካባቢ አስተዳደሮች የድጐማ ገንዘብ የማዘዋወር ኃላፊነት አላቸው (ለወረዳዎችና ለከተማ አስተዳደሮች)::

(3) በአካባቢ ደረጃ የወረዳ የፋይናንስ እና የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች (ወፋኤል)ና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች የተከናወኑ ተግባራትን የዕለት ተዕለት አፈፃፀም የመምራትና የማስተባበር ኃላፊነት ይኖራቸዋል:: እንደ እቅድ፣ ቁጥጥር፣ የፋይናንስ አስተዳደር፣ ክትትል እና ግምገማ የመሳሰሉትን የአፈፃፀም ተግባራት በኃላፊነት ይመራሉ:: ሁሉም ወረዳዎች በየወሩ ከክልሎች ሰለ ተዛወረላቸው ድጎማ ገንዘብ ዘገባ ያቀርባሉ፡ ይህም በአገልግሎት አቅርቦት ኢላማዎች አንጻር የደረሱበትን ያፈጻጸም ዘገባ ያካትታል::

### የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር (አግሚ)

በመንግሥት ዘርፍ ለሚደረጉት ለውጦች በመንግሥት እና በለጋሾች የሚደረጉት ጥረቶች ለመአመ አሰራር ውጤታማነት ወሳኝ ናቸው:: በዚሁ መሰረት የፌዴራል የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር እና የክልል የአቅም ግንባታ ቢሮዎች በመካሄድ ላይ ባለው የኢትዮጵያ የሲቪል ሰርቪስ መሻሻል ፕሮግራም ውስጥ አይነተኛ ኃላፊነት ያለባቸው እንደመሆናቸው መጠን የሚጫወቱትን አይነተኛ ሚና ይቀጥላሉ:: በፌዴራል ደረጃ የሚገኘው የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር እና በክልል እና በአካባቢ ደረጃ የሚገኙት የመስመር ቢሮዎች በክፍል 3 አጠቃላይ ቅንጅትና አፈፃፀም ረገድ እና እንደዚሁም የክፍል 4ትን አንዳንድ ዘርፎች በተመለከተ ከፋይናንስና ከኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በቅርብ ይተባበራሉ (ክፍል 1 ውጤታማ እንዲሆን በማረጋገጡ ረገድ ሁለቱም አስፈላጊች ናቸው):: ይህም እንዲወሰዱ የሚታቀዱ እርምጃዎች አግባብነት ያለው የአቅም ግንባታ ትኩረት የሚሰጥ መሆኑን ለማረጋገጥ ያግዛል:: በተጨማሪም ከብሔራዊ የአቅም ግንባታ ጥረቶች ጋር ተገቢ የሆነ ቅንጅት መኖሩን ያረጋግጣል:: እንደዚሁም ተዛማችነት ባላቸውና በመካሄድ ላይ ባሉ ፕሮግራሞች/እርምጃዎች ልምድ ላይ ለመገንባት ያስችላል::

**የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

የጤናው የምዕተ ዓመት የልማት ግብ አፈፃፀም ገንዘብ የሚተዳደረው በፌዴራል የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር (ጤጥሚ) የእቅድ መምሪያ ይሆናል:: ጤጥሚ የጤና ዘርፉን ግምገማና አፈጻጸም ክትትል የሚያቀናብር የጤና ዘርፍ ማሻሻያ ፕሮግራም(ጤዘማፕ) የተባለ በማዕከል ደረጃ አቋቁሟል፣ ለዚህም መዋቅር የጋራ አስተባባሪ ኮሚቴ (የጋአኮ) እንዲሁም በክልል ደረጃ የክልል የጋራ አስተባባሪ ኮሚቴ (ክጋአኮ) በማቋቋም የጤና ዘርፉን የልማት ፕሮግራም አፈፃፀም ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የሚያስችል ተቋማዊ ማዕቀፍ አዘጋጅቷል:: እነዚህ ኮሚቴች ተግባራቸው በጤናው ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ላይ የምክር አገልግሎት መስጠት፣ መቆጣጠር እና ክትትል ማድረግ ሲሆን የጤናውን የምዕተ ዓመት የልማት ግብ የአፈፃፀም ገንዘብ በበላይነት በመቆጣጠር ተግባራዊ ለማድረግ የሚችሉ ናቸው:: እነዚህ ኮሚቴች በተለይ ጤዘማፕ ተግባራዊነት ክትትልና ግምገማ ላይ ባማካሪነት የሚያገለግሉ ሲሆኑ ሥልጣናቸውን በማሰፋፋት የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ፣ቆሰፎጸ፣ማሰፈጸሚያ ገንዘብ ተግባራዊነት መቆጣጠርንና መከታተልን ሊጨምሩ ይችላሉ:: የሆስፒታልና የጤና ጣብያ ኮሚቴች በአንዳንድ የጤና ተቅዋሞች ተመሥርተው እየሠሩ ነው:: እነዚህ ኮሚቴች የምዕተ ዓመቱ የጤና ኢላማ ድጎማን አፈጻጸም እንዲከታተሉና እንዲገመግሙ ለማብቃት የበለጠ ይጠናከራሉ፡ በተለይም ለተቋሞች በተከፋፈሉት ንብረት/መሣርያ ክምችትና ትክክለኛ አጠቃቀም ቁጥጥር ረገድ:::

**ሌሎች ዋና ዋና የመሥመር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች**: ዋና ዋና የመሥመር የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እና የእነርሱ የክልል፣ የዘርፍ ቢሮዎች እና የወረዳ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በእነርሱ ደረጃ አጠቃላይ የልማት እቅዶች እና በጀቶች ላይ አመራር እና ወይም የቴክኒክ እገዛ ያደርጋሉ:: እነዚህም የሚያካትቱት ከብዙ በጥቂቱ የትምህርት ሚኒስቴርን፣ የግብርና እና የገጠር ልማት ሚኒስቴርን፣ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴርን፣ የፌዴራል የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮን እና የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣንን ነው:: የክልል የዘርፍ ቢሮዎች እና የወረዳ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች የአገለግሎት መገልገያ መረጃ ለሕዝቡ እንዲሰራጭ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል::

**ምክር ቤቶች**: በክልል፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ ምክር ቤቶች በየደረጃቸው የሚገ ኙትን የስራ እቅዶችን እና በጀቶችን የመገምገም እና የማፅደቅ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል:: እንደዚሁም የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ከማድረጋቸው በላይ በመሠረታዊ አገልግሎት አቅርቦት እቅድ እና አስተዳደር ላይ ዜጐች በብዛት እንዲሳተፉ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

**ሌሎች አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች**

ነፃነት እና ቅልጥፍና የተሞላበት አፈፃፀም እንዲኖር ለማድረግ በክፍል 4 ስር ያሉት ተግባራት አጠቃላይ አመራር እና ቅንጅት ከመንግሥት መዋቅር ውጭ ለሚገኝ ድርጅት በኮንትራት መልክ ይሰጣል:: እንደዚህ ያለው ድርጅት በመሰረታዊ አገልግሎት አቅርቦት ጅማሮዎች አፈፃፀም እና ወይም ተጠያቂነት አንፃር የቴክኒክ ችሎታ እና ልምድ ያለው መሆን ይኖርበታል:: ለዓለም ባንክ/ኤምዲቲኤፍ ሪፖርት የሚያደርገው ይህ የሥራ አመራር ወኪል (ሥአወ) ለአጠቃላዩ የፕሮግራም አፈፃፀም፣ የፋይናንስ አስተዳደር እና የእቃ ግዥ የቴክኒክ እገዛ ለመስጠትና ወይም ለማደራጀት ለአቅም ግንባታ፣ ለግንኙነት አውታር እና እንደ አስፈላጊነቱ ድጋፎችን ለማመቻቸት ኃላፊ ይሆናል:: የማህበራዊ ተጠያቂነት የአሰራር ዘዴዎች በሙከራ ደረጃ አግባብነት ባላቸው ድርጅቶች (ያካባቢ ድርጅቶች፣ መያዶች፣ የምርምር ተቋማት፡ አማካሪ... ወዘተ) የሚያከናወኑትን ያቀናጃል፣ ይደግፋል በሌላ መልኩም የተለምዶ ሂደትን ያስተዋውቃል፣ ይከታተላል የሚገኙትንም ውጤቶች ይዘግባል:: ለክፍል 3ና 4 የጋራ የቴክኒክ የሥራ ቡድን (ጋቴሥቡ) ያቋቁማል:: ይህ የቴክኒክ የሥራ ቡድን ያካባቢ ድርጅት ተወካዮችን፣ የመንግሥት ዘርፍ የሥራ ኃላፊችዎንና አግባብነት ያላቸው ለጋሾችን በጋራ እንዲሰባሰቡ ያደርጋል:: የዚህም ዓላማ ከገንዘብ ግልፅነት እና የማኅበራዊ ተጠያቂነት ስራ የሚገኘውን ልምድ ለመገምገም፣ የተገኙ ትምህርቶችን ለማጤን፣ እና ውጤታማ የሆኑ የአሰራር ዘዴችን በይበልጥ ተግባራዊ እንዲደረጉ የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ ነው:: የጋቴሥቡ አላማ፡ ቅንጅት እንዲኖር ለማድረግና፡ በሁለቱ ክፍሎች መካከል የተገኙ ትምህርቶች ወጥነት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥና (ሥአወ) በዚህ ረገድ ከጋቴሥቡ ጋር በቅርብ ግንኙነት የሚያደርግ መሆኑን ማሰረገጥ ነው:: ጋቴሥቡ ከኤምኤ ጋር በመቀናጀት ስራውን በከፍተኛ ደረጃ ለሚገኘው የአስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል::

ይኸው አስተባባሪ ኮሚቴ የሚያካትተው የሲቪል ማኅበረሰብን፣ መንግሥትን (ፌገኤልሚ፣ አገሚ፣ በፌዶች እና ቢሲቢዎችን) እና የልማት አጋሮችን ነው:: በዚሁ መሰረት አስተባባሪ ኮሚቴዉ ወደፊቱ በሚኖረው ሁኔታ ላይ ውይይት ያደርጋል:: እናም አጠቃላይ የሆነ ስትራቴጂካዊ አመራር ይሰጣል:: በተጨማሪም አግባብነት ባላቸው የፖሊሲ ለውጦች ላይ ቅንጅት ያለ መሆኑን እና እንደዚሁም የተለያዩ አጋሮች የሚደገፉት ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች መካከል ቅንጅት ያለ መሆኑን ያረጋግጣል: በዚሁም መሰረት ውይይትን ሊጋብዝ የሚችል የአሰራር ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል:: አስተባባሪ ኮሚቴው የሚዋቀረው በከፍተኛ ደረጃ ሲሆን ለምሳሌ፣ የመንግሥት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን የሚያካትትና ከተለያዩ ቡድኖች የሚመነጨው አባልነት ደግሞ ከቁጥር እና ከአቅም ጋር መቀናጀት ይኖርበታል:: ለመአመ ፕሮጀክት የሚውለው የአያሌ ለጋሾች የድጎማ ገንዘብ በተጨማሪ የመአመ ጉዳዮች ላይ ክትትል የሚያደርግ አነስተኛ የለጋሾች ጽ/ቤት በማቋቋም የሚያስፈልገውን ወጪ ይሸፍናል::

## 7. ዘላቂነት

በፕሮግራሙ በሚደገፈው የስራ ማስኬጃ ወጪ ከፍተኛነት መጠን አይነተኛ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ: ድጋፍ የተሰጠው ፕሮጀክት ከተገባደደ በኋላ የፈጠራቸው አገልግሎቶቹ ዘላቂነት ነው:: ምናልባት የፖለቲካው ሁኔታ የተሻሻለ ከሆነ፣ የለጋሾች እርዳታ እንደሚቀጥል ይጠበቃል: በዚህም መሰረት ድጋፍ ለተሰጣቸው ዘርፎች የዘላቂነት እርዳታ ለማስገኘት የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ እንደሚመጣ ይጠበቃል:: እንደዚህ ባለው ሁኔታ የቀጥታ በጀት ድጋፍ ቢቀጥል ቀደም ሲል በከፍተኛ ደረጃ እንዲጠናከሩ የታቀዱት የልማት ጥረቶች እውን ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ነው:: ምናልባት ሁኔታው አሁን ባለበት ከቀጠለ: ወይም የፖለቲካ ሁኔታው እየተባባሰ ከመጣ: የውጭ የልማት ዕርዳታው: የተዘጋጁት የአገልግሎት አቅርቦቶች የማጠይቁትን የድጋፍ መጠን ለመሸፈን የማይችል ከሆነ: ባንኩ እና አጋሮቹ መንግሥት የተቀነሰውን እርዳታ ለማስተካከል የሚያስችሉትን እርምጃዎች ሊያዘጋጁለት ይሹ ይሆናል: ይህን ሲያደርጉ ግን ለአገልግሎት አቅርቦት የሚያደርጉት ድጋፍ በከፍተኛ ደረጃ ሊቀጥል በሚችልበት መልኩ መሆን አለበት:: ምናልባት መአመ የሚያካሄደውና በክልል መለስ ደረጃ የሚሰጠው ግልጽና ፍትሃዊ የአገልግሎት አቅርቦት ዉጤታማ ሆኖ ከተገኘ: በተመሳሳይ የአሰራር ስልቶች በመጠቀም ድጋፉን ለማጠናከር ቀጣይ የአሰራር ዘዴ ሊቀየስ ይችላል::

ከዚህ ሰፋ ባለ መልኩ መአመ አሰተማማኝነት በሌለበትና የእርዳታ ፍሰት አሰተማማኝ ባልሆነበትና የፍሰቱ ትንበያ ዝቅተኛ በሆነበት ሁኔታ ላይ የተፈጠረ አማካይ ዝግጅት ነው:: አፈፃፀሙም ከተጀመረ በኋላ በክልል ደረጃ የሚደረጉ የአገልግሎት አቅርቦቶችን ድጋፍ ለማሻሻል እና የአካባቢ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የመአመን የሥራ አፈፃፀም መገምገም ታስቧል:: በዚህም መሥረት መንግሥትና የልማት አጋሮቹ መአመ እንዳለ ይቀጥል ወይም አንዳንድ የመአመ አሰራሮች ይሻሻሉ ወይንም ከመአመ አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ ፋይዳዎችን የፋይናንስ ሂደታቸውን ወደ ጎን በመተው ወደ ቀጥታ የበጀት ድጋፍ እንመለስ የሚሉት ላይ ዉሳኔ መስጠት አለባቸው::

## 8. ቀደም ብለው በአገሪቱ በዘርፉ ከተደረጉት እንቅስቃሴዎች የተቀሰሙ ልምዶች

የታቀደው ፕሮጀክት ዝግጅት ዓለም አቀፍ ልምዶችንና እንደዚሁም በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ሰላለው ወቅታዊ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ሁኔታ በተካሄዱ ጥናቶች ላይ ተመሥርቷል::

<u>ከዓለም አቀፍ ልምድ የተቀሰሙ ትምህርቶች</u>

- ያለው ልምድ የሚያሳየው የመልካም አስተዳደር እጦት ችግር በሚከሰትበት ወቅት የመሰረታዊ ማኅበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ዕጥረት እንዳይባባሰ የማድረጉን አስፈላጊነት ያበሰራል: በተጨማሪም በተቻለ መጠን የድህ-ደገፍ አገልግሎቶችን አቅርቦት በማንኛውም ምንገድ ማፋጠን እንደሚያሰፈልግ ነው::
- ማኅበራዊ ውጥረት በሰፈነበት ወቅት ለማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት ትኩረት መስጠት ከፍተኛ የሆነ ግልፅነት እና ተጠያቂነት በመንግሥት የአገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል::

ይህም በበኩሉ የአካባቢ የአስተዳደር አካላትንና ዜጐችን የስልጣን ባለቤት በማድረግ ለዘለቄታው የዲሞክራሲያዊ ሁኔታ እንዲፈጠር አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

- አጠቃላይ የበጀት ድጋፍ ከሚሰጣቸው ሌሎች የአሰራር ዘዴዎች ላይ የተገኙት የልዕቡ የጋራ ግምገማ ትምህርቶች እንደሚያሳዩት (እንደመአመ) የመሳሰሉት ተግባራዊ ሊሆኑ ከማይችሉ ግቦች አኳያ በተለይ በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ ፕሮግራሞቹ ከአቅማቸው በላይ ጭነት እንዲሸከሙ ማድረጉ አላስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በዚሁ መሰረትም ለድሆች የሚሆን ወጪን በተመለከተ ስፋት ያላቸውን እና በይበልጥ ጥራት ያላቸው አተረጓጐሞች ትኩረት እንዲሰጣቸው ማድረጉ አስፈላጊ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

<u>ከኢትዮጵያ ተለምዶ የተቀሰሙ ትምህርቶች</u>

በኢትዮጵያ የቀጥታ የበጀት ድጋፍ አፈፃፀምን በተመለከተ በክልል ደረጃ ለውጥን ለመደገፍ በቂ የሆነ የአሰራር ስልት ማዘጋጀት አስቸጋሪ መሆኑን የተገኘው ትምህርት ያመለክታል፡፡

- በሌላ በኩል ደግሞ በልማት አጋሮች እና በክልል/በአካባቢ አስተዳደሮች መካከል ግንኙነቶችን ለመፈጠር አግባብነት ያላቸውን የአሰራር ዘዴች ለማቅረብ አልተቻለም፡፡

- በኢትዮጵያ ከቀጥተኛ የበጀት ድጋፍ ማዕቀፍ አኳያ አይነተኛ የውይይት መሳሪያዎች እና የለጋሾች ቅንጅት ዘዴዎች ሊፈልቁ ችለዋል፡፡ ሌላው የተገኘው ትምህርት በተለያዩ መማርያዎችና ፕሮግራሞች ላይ ጽኑነት አስፈላጊ መሆኑን ነው(ለምሳሌ፣ በአመልካቾችና ስምምነት በተደረሰባቸው እርምጃዎች)
- ከተመረጡ ክልሎች ጋር የበጀት ድጋፍ በማድረግ እና አብሮ በመስራት የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው ለጋሾች ልምድ እንደሚያሳየው ከክልል አስተዳደሮች ጋር በይበለጥ በቀጥታ የመስራቱ ሁኔታ በልማት እና በአገልግሎት አቅርቦት ለውጦች ላይ ውጤታማ የሆነ ትብብር እንዲፈጠር የሚያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ልምድ በፌድራል ደረጃ ያሉት ፖሊሲዎች በአካባቢ ደረጃ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ በጐ ተፅእኖ እንዳላቸው ያሳያል፡፡ በመሆኑም ከክልል መለሰ አሰተዳደሮች ጋር የሚደረገው ግንኙነት በፌዴራል ወይም በክልል መድረክ ላይ ለሚደረገው የፖሊሲ ውይይትን ሊተካ እንደማይችል ነው የሚያሳየን፡፡

- ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሁለት ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከክልልና ክልል መለሰ አሰተዳደሮች ጋር እንደዚሁም ከሲቪል ማህበረሰብ ጋር የሚደረግን ውይይት መደገፍ የተሻለ መሆኑ በጣም ግልፅ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የቀጥታ የበጀት ድጋፍ ሲደረግ በነበረበት ጊዜ ከተገኘው ውጤት ጋር ሲነፃፀር ሁኔታው ለመአመ አሰራር አይነተኛ ፈተና እንደሚሆን ነው፡፡

- ከሲኤፍኤ እና ከሲፒኤአር ጋር ከዲኤፍአይዲ ኢሲና ባንኩና ከሌሎች በኢትዮጵያ ከሚገኙ የልማት አጋሮች ጋር የተደረገው የአስር አመት የመንግሥት ወጪ ግምገማ እንደሚያመለክተው የአገልግሎት ወጪዎችን ለመሸፈን ከመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደርና የግምጃ ቤት አሰራር ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከርና አብሮ መስራቱ በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን ነው የሚያመለክተው፡፡

## 9. ፖሊሲዎችን መንከባከብ (ሕዝባዊ ምክክሮችን ጨምሮ)

**ጥቅም ላይ የዋሉ የሕክምና ቁሳቁሶችንና እና መሳሪያዎችን ማስወገድ፣**
ክትባቶችን በተመለከተ እንደገና ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ለማድረግ እና የኤችአይቪ/ኤድስ መተላለፊ እንዳይኖር እና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች እንዳይተላለፉ ለማድረግ መርፌዎችን በጥሩ ሁኔታ የማስወገዱ ጉዳይ ሊጠቀሰ ይገባል፡፡ ጠንቃቃ አያያዝ እና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች ካልተወሰዱ በስተቀር ጥቅም ላይ የዋሉ የሕክምና እቃዎች እና መሳሪያዎች ከባድ የጤና አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

ጥቅም ላይ የዋሉ የሕክምና እቃዎች እና መሳሪያዎች አግባብነት በሌለው ዘዴ መያዙ የሚያስከትላቸውን ጠንቅ በመገንዘብ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጥንቃቄ ጉድለት እና በአያያዝ ጉድለት ምክንያት ጥቅም ላይ የዋሉ የሕክምና መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶች የጤና አደጋ እንዳያስከትሉ የሚያስችል መመሪያ በመስከረም 1990 ዓ.ም. አውጥቷል፡፡

መመሪያው አይነተኛ የሆኑትን የሕክምና መሳሪያዎችና የቁሳቁስ አይነቶችን፡ በሕክምና፡ ፓቶሎጂካል፡ ኬሚካል፡ ተላላፊ፡ ባዮሎጂካል፡ ፋርማሰቲካል፡ ፍሳሽ በማለት ዘርዝሮ በማስቀመጥ በጤና ተቋማት መወሰድ ያለበትን እርምጃዎች ያሰቀምጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ የመርፌ አወጋግ መመሪያ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ያለው መመሪያ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ጥቅም ላይ የዋሉ የሕክምና መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶችን በአግባቡ ለመያዝ እና አገልግሎት ላይ ለማዋል በቂ ጥንቃቄዎች ማድረግ እንደሚያሰፈልግ ያሳሰባል፡ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መሆኑንም በየጊዜው ይገመግማል፡፡ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የጤና መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶች በጤና ተቋማት በተገቢው መንገድ ሊያዙ እና ሊወገዱ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚያመለክተው በአማርኛ የተፃፈው የመንግሥት መመሪያ በመንግሥት በኩል እንደእነዚህ ያሉ አገልግሎቶችን ለሚያቀርቡ የጤና ተቋማት በሰፊው እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ በቅርቡ ደግሞ (በየካቲት ወር 1998) የዚሁ ሰነድ የእንግሊዘኛ ትርጉም ለዓለም ባንክ የመረጃ ቢሮ ደርሷል፡፡

**9. ግንኙነት ለማድረግ**

**ጂል አርምስትሮንግ**
**የኃላፊነት ደረጃ፡ የአገር ፕሮግራም አስሪባባሪ**
**ስልክ፡ (202) 473-8471**
**ፋክስ፡ (202) 473-5453**
E-mail: Jarmstrong@worldbank.org

**10. ለበለጠ መረጃ ከዚህ በሚከተለው አድራሻ ይጠይቁ**

**የመረጃ ቢሮ**
**የዓለም ባንክ**
**1818 ኤች ስትሪት፣ ኤንደብሊዩ**
**ዋሽንግቶን ዲሲ 20433**
**ስልክ፡ (202) 454-5454**
**ፋክስ፡ (202) 522-1500**